መመሪያ ቁጥር 2 /2010 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ቢሮ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 እና ደንብ ቁጥር 159/2010 ለማስፈጸም የወጣ የገጠር መሬት አጠቃቀም መመሪያ

የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 ዓ.ም ተከትሎ በወጣው ደንብ ቁጥር 159/2010 ዓ.ም እንዳንድ ድንጋጌዎች በመመሪያ እንዲመለሱ በተወሰነው መሰረት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሄራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ተሻሽሎ በወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252/2009 ዓ.ም አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ አዋጅ ቁጥር 252/2009 ዓ.ም እና ተከትሎ የወጣውን ደንብ ቁጥር 159/2010 ዓ.ም ለማስፈፀም የወጣ የገጠር መሬት አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 2 /2010 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 252/2009 እና በደንብ ቁጥር 159/2010 የተሰጡ ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያም እኩል ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

3. ዓላማ

መመሪያዉ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. በአዋጁና ደንቡ ውስጥ የተዘረዘሩት የገጠር መሬት ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች የተለያዩ መብቶችና ግዴታዎች በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግና፤
2. የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮም ሆነ በተለያዩ እርከኖች በተዋረድ የሚገኙ አካላቱ ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ እንዲወጡ በማድረግ ዘላቂ፣ በህበረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለዉና በኢኮኖሚ አዋጭ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ስርዓት እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፡፡

4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአማራ ብሄራዊ ክልል ውስጥ በሚገኝ የገጠር መሬት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

ተዘጋጅቶ ከተሰጠው የመሬት አጠቃቀም እቅድ ውጭ በሆነ የአጠቃቀም ዓይነት በሚጠቀሙ እና እቅድ ባልተሰራባቸው ቀበሌዎች የሚኖሩ ባለይዞታዎች በወቅታዊው አጠቃቀም ላይ ለውጥ ቢያደርጉ የሚወሰድ እርምጃ

5. ተዘጋጅቶ ከተሰጠው የመሬት አጠቃቀም እቅድ ውጭ በሆነ የአጠቃቀም ዓይነት በሚጠቀሙ የመሬት ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች ላይ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት እርምጃዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

5.1 የመሬት አጠቃቀም ዕቅዱን ያላግባብ በመቀየር ሲጠቀም የተገኘ ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ፣ በሚመለከተው አካል ተዘጋጅቶ በተሰጠው የአጠቃቀም እቅድ መሰረት ቀይሮ እንዲጠቀም የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ በቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ግብረ ኃይል ይሰጠዋል፤

5.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5.1) በተሰጠው የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ መሰረት በ15 ቀን ውስጥ የመሬት ባለይዞታው ወይም ተጠቃሚው ስህተቱን ካላረመ፣ በቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ግብረ ኃይል ዓማካኝነት በህግ አግባብ ታቅዶ ወደ ነበረው የመሬት አጠቃቀም ዓይነት እንዲመለስ ወይም እንዲስተካከል ያደርጋል፤

5.3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (5.2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአጠቃቀም ግድፈቱን በ15 ቀን ዉስጥ በቀበሌው ግብረ ኃይል መስተካከል የማይቻል ሆኖ ከተገኘ መረጃዉን በማደራጀት በግብረ-ኃይሉ ወይም በወረዳው ግ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት ዓማካኝነት በባለይዞታው ወይም በተጠቃሚው ላይ በፍትህ ጽ/ቤት በኩል ክስ እንዲመሰረትበት ይደረጋል፡፡

6. የመሬት አጠቃቀም እቅድ ባልተሰራባቸው ቀበሌዎች የሚኖሩ ባለይዞታዎች በነባሩ ወይም በወቅታዊው አጠቃቀም ላይ ለውጥ ቢያደርጉ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የእርምት እርምጃዎች እንደየአግባብነታቸው ስልጣን ባለው አካል ይወሰዱባቸዋል፡፡

በጥናት ላይ ተመስርቶ ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም የገጠር መሬት ይዞታ ላይ ገቢራዊ በመደረግ ላይ ያለ ወቅታዊ የአጠቃቀም ዕቅድ በዘፈቀደ መቀየር እንደማይቻልና የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ተብለው ከተመረጡት ስፍራዎች ውጭ በእርሻ፣ በግጦሽ፣ በወልና በደን መሬቶች ላይ ማናቸውንም አዲስ ግንባታ ማካሄድ የተከለከለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በመደንገጉ ይህን ድንጋጌ በሚጥስ የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የእርምት እርምጃዎች ይወሰዱበታል፡፡

6.1. ነባሩን የመሬት አጠቃቀም ዓይነት የቀየረ ባለይዞታ ወደ ቀድሞው የአጠቃቀም ዓይነት እንዲቀይር ለማስቻል በቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ግብረ ኃይል ለባለይዞታው ወይም ለተጠቃሚው የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

6.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6(1) መሰረት በተሰጠው የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ ባለይዞታው ወይም ተጠቃሚው በ15 ቀናት ወስጥ አጠቃቀሙን ወደ ነበረበት የአጠቃቀም ዓይነት ካልቀየረ ወይም ስህተቱን ካላስተካከለ የቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ግብረ ኃይል ወደ ቀድሞው የመሬት አጠቃቀም አይነት እንዲመለስ ወይም እንዲስተካከል ያደርጋል ወይም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡

6.3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (6.2) በተደነገገው መሰረት የአጠቃቀም ለውጡን በ15 ቀን ዉስጥ በቀበሌው ግብረ ኃይል ለማስተካከል የማይቻል ሆኖ ከተገኘ፣ መረጃዉን በማደራጀት በወረዳው ጽ/ቤት ዓማካኝነት በፍትህ ጽ/ቤት በኩል ክስ እንዲመሰረትበት ይደረጋል፡፡

ክፍል ሦስት

የገጠር መሬት የይዞታ መብት ስለሚታጣባቸዉ ሁኔታዎች

7. ይዞታውን በተዘጋጀው የመሬት አጠቃቀም እቅድ አለማልማትና ይኸው እቅድ ባልተዘጋጀላቸው አካባቢዎች ደግሞ መሬቱን በእንክብካቤ ያልያዘ ባለይዞታና ተጠቃሚን በተመለከተ

በአዋጁ አንቀጽ 21 ንኡስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር "ሠ" መሰረት ይዞታውን በተዘጋጀው የመሬት አጠቃቀም እቅድ አለማልማትና ይኸው እቅድ ባልተዘጋጀላቸው አካባቢዎች ደግሞ መሬቱን በእንክብካቤ ያልያዘ ባለይዞታና ተጠቃሚ ከዚህ በታች በተመለከተዉ ቅደም ተከተል መሰረት ይዞታዉንና የመጠቀም መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡

7.1. በማሳ ደረጃ ተዘጋጅቶ የተረከበዉን የመሬት አጠቃቀም እቅድ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተግባራዊ ባላደረገ ባለይዞታና ተጠቃሚ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አማካኝነት ይሰጠዋል፡፡

7.2. በተሰጠዉ የመጀመሪያ ደረጃ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መሰረት ጥፋተኛው ከስህተቱ ሊታረም ያልቻለ እንደሆነ ወይም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያልጀመረ እንደሆነ፣ ለሁለተኛ ጊዜ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ይሰጠዋል::

7.3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7.1) እና (7.2) በተደነገገው መሰረት ተከታታይ ማስጠንቀቂያዎች ከተሰጡት በኋላ ጥፋተኛው ያንኑ ጥፋት እንደገና መፈፀሙ የተረጋገጠበት እንደሆነ፣ ያፈራውን ንብረት አንስቶ ይዞታውን ከነአካቴው እንዲለቅ በወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና

አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ይወሰንበታል፤ መሬቱም ወደ መሬት ባንክ ገቢ ይደረጋል፡፡

7.4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (7.3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማስጠንቀቂያው እስከ ተሰጠው ጊዜ ድረስ በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ ማሻሻያና ሊነሳ በማይችል በመሬቱ ላይ ላለማው ንብረት አግባብ ባለው የካሳ ህግ መሰረት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ ሊከፈለው ይችላል፡፡

7.5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7.1) እና (7.2) የተደነገገው ቢኖርም በእያንዳንዱ የማስጠንቀቂያ ጊዜ መካከል ቢያንስ አንድ የሰብል ዘመን ቆይታ እንዲኖር ይደረጋል::

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. ስለተሸሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

9. መመሪያውን የማሻሻል ስልጣን

የአማራ ብሄራዊ ክልል ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

10. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር

ሰኔ 1 ቀን 2010 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ